በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን መጋቢት 1 8 2012
Date
ቁጥር 4/0646/12
Ref.No.

ለየጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት፣

ጉዳዩ፡- የዕቃዎች የመጋዘን ቆይታ ጊዜ ገደብ ስለማራዘም፣

በጉምሩክ አዋጁ ማሻሻያ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 13(1) እና (2) ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀን፣ ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአሥር ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፃሞበት መውጣት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 2(13)(11) የመጋዘን ቆይታ የተወሰኑ ጊዜ ገደቦችን በበቂ ምክንያት ኮሚሽኑ ሊያራዝም እንደሚችል በተደነገገውና በተሰጠው ስልጣን መሠረት የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ገደብ ስለሚራዘምበት ሁኔታ የሚመራበት አሰራር በቁጥር 4/04/24/12 በቀን 22/02/2012 ዓ.ም. ሰርኩላር በማስተላለፍ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ አደጋ ምክንያት የገቢና ወጪ ዕቃዎች ፍሰትን፣ ዕቃዎች ከጉምሩክ ወደቦች በጊዜ መውጣት ያልቻሉበት መንስኤን፣ የንግድ ሁኔታ መቀዛቀዝን፣ የሰዎች እንቅስቃሴ መገደቡን እንዲሁም በ15/07/12 የሚኒስትሮች ም/ቤት ባስተላለፈው ውሳኔ መነሻ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች በተወሰነ ደረጃ በመገደባቸው በአዋጁ ማሻሻያ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 13(1) እና (2) ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃዎች ከወደቦች በጊዜ ገደቡ መውጣት አለመቻላቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡



☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

ስለሆነም በጉምሩክ አዋጅ ማሻሻያ 1160/2011 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 13(1) እና (2) የተደነገገው የ15 ቀናት የደረቅ ወደብ የቆይታ ጊዜ እና የ10 ቀናት የአየር መንገድ የመጋዘን የቆይታ ጊዜን በማስመልከት ቀደም ሲል በኮሚሽኑ በተላለፈው ሰርኩላር መሠረት ለማስተናገድ በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ አደጋ ምክንያት በተፈጠረው አስገዳጅ ሁኔታ በሰርኩላሮቹ በተደነገጉ ምክንያቶች ብቻ ማስተናገድ የማያስችል ሁኔታ በመፈጠሩ በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮችን ጨምሮ አገር ውስጥ ገብተው የትራንዚት ማጠናቀቂያ በመፈፀም በጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘኖች የገቡና የሚገቡ ገቢ ዕቃዎች በሙሉ የኮሮና ወረርሽኝ ችግር መወገዱ እስከሚረጋገጥ ድረስ ያለ ቅጣት እንዲስተናገዱ በአዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 2 (13)(11) መሠረት የተወሰነ ስለሆነ ያለ ምንም ምክንያትና እንግልት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች አስመጪዎች በሙሉ ፈጣን አገልግሎት እንድትሰጡ ሆኖ በዚሁ አግባብ አገልግሎት የተሰጠባቸው ሰነዶች ለብቻ ተመዝግበው እንዲያዙና በየወሩ ለኮሚሽኑ ዋና መ/ቤት የፅሑፍ ሪፖርት እንዲቀርብ በጥብቅ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 1
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.1

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>፣-

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

  <u>አዲስ አበባ</u>፣
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለዕቃ አወጣጥ ዳይሬክቶሬት

  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>